ስርዓት

Fairview Health Services (ፌርቪው የጤና አገልግሎቶች)።

**ፖሊሲ**

# የታካሚ የፋይናንስ አገልግሎቶች የሂሳብ አከፋፈል እና አሰባሰብ የሂሳብ አከፋፈል እና አሰባሰብ ፖሊሲ

*የታተሙ ቅጂዎች ለዋቢነት ብቻ የሚውሉ ናቸው። የቅርብ ጊዜውን እትም ለማግኘት እባክዎን የኤሌክትሮኒክ ቅጂውን ይመልከቱ።*

**ዓላማ:**

ይህ ፖሊሲ በ Fairview ለቀረበ የሕክምና እንክብካቤ ክፍያ ሳይፈጸም ሲቀር ሊወሰዱ የሚችሉ፣ እንደ ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎች ያሉ የ Fairview Health Services እና የ HealthEast (በጥቅሉ "Fairview" የሚባሉ) የታካሚ የሂሳብ አከፋፈል ሂደትን እና የመሰብሰብ እርምጃዎችን ይገልጻል። ከዚህ ፖሊሲ በስተጀርባ ያሉት መርሆዎች ሁሉንም ታካሚዎች እና ሀላፊነት የሚሰማቸው ዋስትና ሰጪዎችን (ከዚህ በኋላ "ታካሚ(ዎች)" ተብሎ የሚጠራ) በእኩልነት እና በአክብሮት መያዝ፣ ተገቢ የሆኑ የሂሳብ አከፋፈል እና አሰባሰብ ሂደቶችን ወጥ በሆነ መንገድ መከተልን ማረጋገጥ፣ እንዲሁም ታካሚው በ Fairview የፋይናንስ እርዳታ ፖሊሲ (ከዚህ በኋላ "FAP" ተብሎ የሚጠራ) መሰረት እርዳታ ለማግኘት ብቁ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ተገቢ ጥረቶች መደረጋቸውን ማረጋገጥ ናቸው።

**የፖሊሲ መግለጫ፡**

ታካሚዎቻችን አገልግሎት ካገኙ በኋላ ታካሚዎች እና የሚመለከታቸው ከፋዮቻቸው በወቅቱ እና ትክክለኛ በሆነ መንገድ እንዲከፍሉ ማድረግ የ Fairview ፖሊሲ ነው። በዚህ የሂሳብ አከፋፈል እና አሰባሰብ ሂደት ወቅት፣ የ Fairview ሠራተኞች ጥራት ያለው የደንበኞች አገልግሎት ለመስጠት እና በሁሉም ያልተከፈሉ ሂሳቦች ላይ ወቅታዊ ክትትል ለማድረግ በቁርጠኝነት ይሠራሉ። በተጨማሪም የ Fairview ሠራተኞች፣ አንድ ታካሚ በ FAP መሰረት የገንዘብ እርዳታ ለማግኘትት እጩ መሆኑን ሊጠቁሙ የሚችሉ ምክንያቶችን በንቃት የሚከታተሉ ሲሆን በዚህ ሂደትም ታካሚዎችን ይረዳሉ።

**ትርጓሜዎች፡**

**ECAs** – ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎች፡ የሚከተሉትን የአሰባሰብ እንቅስቃሴዎች ያካትታሉ፡

- በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች ውስጥ የታካሚን ዕዳ ለሌላ አካል መሸጥ።
- አንድን ታካሚ በተመለከተ ለክሬዲት ኤጀንሲ አሉታዊ የክሬዲት መረጃ ሪፖርት ማድረግ።
- ቀደም ብሎ ባልተከፈለ ሂሳብ ምክንያት በአሁን ወቅት ከህክምና አንፃር አስፈላጊ የሆነ እንክብካቤን ማዘግየት ወይም መከልከል ወይም በወቅቱ ከህክምና አንፃር አስፈላጊ የሆነ እንክብካቤ ከመሰጠቱ በፊት ያልተከፈለው ቀዳሚ ሂሳብ እንዲከፈል መጠየቅ።
- የንብረት መያዝ፣ የደመወዝ እገዳ፣ የባንክ ሒሳብ እገዳ ወይም መያዝ፣ የፍትሐ ብሔር እርምጃ መከተል እና ሌሎች የተወሰኑ ሕጋዊ እርምጃዎችን ጨምሮ ሕጋዊ ወይም የፍርድ ሂደት የሚጠይቁ እርምጃዎች።

**አስፈላጊ ሕክምና**

ከሕክምና አንፃር አስፈላጊ የሆነ እንክብካቤ ማለት፣ በ Fairview ዕውቅና በተሰጠው የሕክምና ሐኪም/የሕክምና ባለሙያ አመለካከት እና በመደበኛ የእንክብካቤ ደረጃ መሰረት የሚከተሉትን ለማድረግ አሳማኝ በሆነ መልኩ የሚያስፈልግ የሕክምና ክትትል ነው፡-

- የሕመም፣ የጤና ሁኔታ ወይም የአካል ጉዳት እንዳይከሰት ወይም እንዳይባባስ ለመከላከል፤
- ምርመራ ለማድረግ፤
- ለአካላዊ፣ ባህሪያዊ እና/ወይም ለአዕምሮ ጤና ሁኔታ የፈውስ፣ ህመምን የማስታገስ፣ ወይም ተሃድሷዊ ህክምና ለመስጠት፤ እና/ወይም
- የግለሰቡን እና በተመሳሳይ ዕድሜ ላይ ለሚገኙ ሰዎች አስፈላጊ የሆኑትን የማከናወን አቅሞች ከግምት ውስጥ በማስገባት ግለሰቡ የዕለት ተዕለት ተግባሩን ለማከናወን እንዲችል ወይም የማከናወን አቅምን እንዲጠብቅ ለማገዝ።
- ከህክምና አንፃር አስፈላጊ የሆነ እንክብካቤ የሚያካትተው በፌዴራል ማህበራዊ ዋስትና ሕግ በ Title XIX ሥር በተደነገገው መሠረት አስፈላጊ የሆኑ የውስጥ ታካሚ እና የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች፣ እንዲሁም በፌዴራል የማኅበራዊ ዋስትና ሕግ ክፍል በ Title XVIII ሥር በተደነገገው መሠረት ለጤና አስፈላጊ ነው ተብሎ የሚታሰበውን ማንኛውንም የውስጥ ታካሚ እና የተመላላሽ

ታካሚ የሆስፒታል አገልግሎት ነው። ከዚህም በተጨማሪ፣ ሆስፒታሉ ካፒታል ወይም ትርፍ ጥቅም በሚያስገኝበት አጋርነት ወይም በ LLC በሆስፒታሉ ተቋም ውስጥ የሚሰጥ እንክብካቤ ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ነው። አገልግሎቶች በሚሰጡበት ጊዜ በአብዛኛው ተቀባይነት ባላቸው አገራዊ የሕክምና ደረጃዎች መሠረት መከናወን አለባቸው። እያንዳንዱ አገልግሎት ዓላማውን በተገቢው ለማሳካት በመጠን፣ በሚቆይበት ጊዜ እና በአገልግሎት አድማስ በቂ መሆን አለበት።

- ከህክምና አንፃር አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶች በሙከራ ደረጃ የሚሰጡ ወይም በባህሪያቸው መዋቢያ የሆኑትን የሚያካትቱ አይደሉም።
- በጣም አስፈላጊ የሆኑ የሕክምና ዓይነቶችን የሚደግፉ ሌሎች ሁኔታዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡
  - ይህ ሁኔታ ያለባቸው ታካሚዎች ከተጠየቀው ሕክምና ተጠቃሚ እንደሚሆኑ የሚያረጋግጥ ከፍተኛ ጥራት ያለው ሳይንሳዊ ማስረጃ፤
  - የጥቅሙ ዓይነት ከህክምና አንፃር ጉልህ ስፍራ የሚሰጠው ሲሆን፤ እና/ወይም
  - ብዙ ወጪ የማይጠይቁ አማራጭ ሕክምናዎች እና የአስተዳደር መስመሮች ከግምት ገብተው ውድቅ ሲደረጉ።

**የሙከራ ሕክምናዎች**

በሙከራ ደረጃ የሚሰጡ ሕክምናዎች የጤናውን ሁኔታ በምርመራ ለይቶ በማወቅ፣ በመከላከል እና በማከም ረገድ አግባብነት ባለው መስክ በሚሠሩ ባለሙያዎች በአብዛኛው አስተማማኝ እና ውጤታማ ሆነው ያልተገኙ ሕክምናዎች እና የምርመራ ሂደቶች ናቸው። አንድ ሕክምና የሙከራ እንደሆነ በሚወሰንበት ጊዜ፣ አግባብነት ያላቸው ምክንያቶች በዚህ ባይገደቡም የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፦

- ሕክምናው የክሊኒካል ጥናት ክፍል ብቻ ሆኖ መገኘቱ ወይም አለመገኘቱ፤
- በአቻ በተገመገሙ ጆርናሎች ውስጥ ያሉ አግባብነት ያላቸው ጽሁፎች ሕክምናው ላይ እየታየ ላለው የጤና ሁኔታ ተጨማሪ ጥናት እንዲደረግ ጥሪ ማቅረባቸው፤ ወይም
- ሕክምናው በተለየ የሰውነት አካል አካባቢ ላይ፣ ጉልህ በሆነ መልኩ በተለየ መንገድ እና/ወይም ለተለየ የጤና ሁኔታ ጥቅም ላይ መዋሉ፣ ከዚያም በአጠቃላይ አግባብ ባለው መስክ [በ Fairview፣ በትዊን ሲቲ፣ ሚኒሶታ፣ ዩ.ኤስ፣ ወዘተ ውስጥ] ባሉት ሌሎች ባለሙያዎች ተቀባይነት ማግኘቱ።

**ከፋይናንስ አንፃር ለመቋቋም የሚከብድ ሸክም**

አገልግሎቱን ለማቅረብ ለ Fairview ከግብር ነፃ የሆነ አካል ከፍተኛ ወጪ የሚኖርበት ሁኔታ እና ለአገልግሎቱሊኖሩ ለሚችሉ የታካሚ ፍላጎት ተቋሙ ተመሳሳይ ሁኔታ ላላቸው ሁሉም ታካሚዎች በቂ ክፍያ ሳይደረግ ተመሳሳይ አገልግሎት መስጠት እና በፋይናንስ ረገድ ብቁ ሆኖ መቀጠል በማይችልበት ክስተት።

**ቤተሰብ**

ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ፣ ቤተሰብ የሚባለው:

- በ IRS መመሪያዎች በተገለጸው መሰረት፣ ባለትዳር የሆኑ ጥንዶች እና ማናቸውም በእነሱ ስር የሚኖሩ ጥገኛ ሰዎች።
- በ IRS መመሪያዎች በተገለጸው መሰረት ጥገኛ የሆኑ ሰዎች ያሉት አንድ ግለሰብ።
- ምንም ዓይነት ጥገኛ የሆኑ ሰዎች የሌሉት ያላገባ ሰው።

ቤቱ ከአንድ በላይ ቤተሰብ የያዘ ከሆነ የድህነት መመሪያዎች ለእያንዳንዱ ቤተሰብ በተናጠል ተግባራዊ ይደረጋሉ።

**የአሠራር ሂደት፡**

I. የታካሚ ሂሳብ አከፋፈል፡

ሁሉንም የመድን ክፍያ ጥያቄዎችን በትክክል እና በወቅቱ እንዲከፍሉ ማድረግ የ Fairview ዕቅድ ነው። ምንም እንኳ በታካሚዎች እና ከፋዮች መረጃ እና ግንኙነት ላይ የሚመሰረት ቢሆንም፣ Fairview ታካሚዎች ትክክለኛ የሂሳብ እና የክፍያ መክፈያ መረጃ እንዲያገኙ እንዲሁም ክፍያ የመፈፀም እና/ወይም ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ የማመልከት ዕድል እንዲኖራቸው በቂ የክትትል አገልግሎት ይሰጣል። የሂሳብ አከፋፈሉ ሂደት በሚከተሉት መመሪያዎች ይታገዛል፦

A. ለሁሉም ዋስትና ላላቸው ታካሚዎች Fairview ከሚከተለው በስተቀር ሁሉንም ሶስተኛ ወገን ከፋዮችን (በታካሚው በቀረበው ወይም በተረጋገጠው መሰረት) በወቅቱ የሚያስከፍል ይሆናል።
   - ከአገር ውጭ ያለ መድን - በታካሚው ጥያቄ ለመድን ዋስትናቸው የሚሰጡት የክፍያ መጠየቂያ ግልባጭ ለታካሚው ይሰጣል። Fairview በ 90 ቀናት ውስጥ ከታካሚው ክፍያ ይጠብቃል። Fairview፣ በራሱ ውሳኔ፣ እንደየሁኔታው፣ ለታካሚው ያለውን አክብሮት ለማሳየት የክፍያ መጠየቂያውን ከአገር ውጭ ላለው መድን መላክን ሊመርጥ ይችላል።

B. በአሁኑ የዐቃቤ ሕግ አጠቃላይ የአሰባሰብ ደንቦች ስምምነቶች መሰረት በሆስፒታል የሚሰጡ ከህክምና አንፃር አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚያገኙ በሚኒሶታ ወይም በዊስኮንሲን የሚኖሩ ማንኛውም የመድን ሽፋን የሌላቸው ታካሚዎች የመድን ሽፋን

ለሌላቸው የሚደረግ የዋጋ ቅናሽ ያገኛሉ። የመድን ሽፋን ለሌላቸው የሚደረገው የዋጋ ቅናሽ መንግስታዊ ላልሆነው ትልቁ ተቋራጭ ከፋያችን ከሚሰጠው ቅናሽ ጋር እኩል የሚሆን ሲሆን ማንኛውም ቀሪ ሂሳብ በተለመደው የ Fairview የአከፋፈል ሂደት በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ በታካሚው የሚከፈል ይሆናል። ሁሉም ታካሚዎች በማንኛውም ጊዜ ለሂሳባቸው የተብራራ መግለጫ መጠየቅ ይችላሉ።

C. በ Fairview ስህተት ምክንያት የክፍያ ጥያቄ በከፋዩ ቢከለከል (ወይም ባይከወን) Fairview ከፋዩ የክፍያ ጥያቄውን ከፍሎ ቢሆን ኖሮ ታካሚው ተጠያቂ ከሚሆንበት መጠን በላይ ታካሚውን አያስከፍልም።
D. ከ Fairview ቁጥጥር ውጭ በሆኑ ምክንያቶች አንድ የክፍያ ጥያቄ ውድቅ ከተደረገ (ወይም ካልተከወነ) የ Fairview ሠራተኞች የክፍያ ጥያቄውን በተመለከተ መፍትሄ ለማመቻቸት በሚያስችል ሁኔታ ከከፋዩ እና ከታካሚው ጋር ክትትል ያደርጋሉ። የክፍያ ጥያቄውን በተመለከተ ምክንያታዊ የሆኑ የክትትል ጥረቶች ከተደረጉ በኋላ መፍትሄ የማይመጣ ከሆነ፣ Fairview የክፍያ መጠየቂያውን ለታካሚው ሊልክ ወይም ከወቅቱ የ Fairview ምርጥ የአሰራር ደረጃዎች ጋር የሚጣጣሙ ሌሎች እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል።
E. የክፍያ መጠየቂያ የደረሳቸው ሁሉም ታካሚዎች ከፋይናንስ ነክ እርዳታ ጋር በተገናኘ ከ Fairview ጋር የመገናኘት ወይም በክፍያ ሂደቱ በማንኛውም ጊዜ ስለ ሂሳባቸው የክፍያ ዝግጅት የመወያየት አጋጣሚ ይኖራቸዋል።

II. የታካሚ አሰባሰቦች እና የኤጀንሲ አሰባሰቦች፡

A. ለራስ-ክፍያ ሂሳቦች አሰባሰብ ወደ እያንዳንዱ ታካሚ የመጨረሻ የሚታወቅ አድራሻ በደብዳቤ ወይም በኢሜይል ቢያንስ 3 የተለያዩ መግለጫዎች መላክ አለባቸው፤ ሆኖም አንድ ታካሚ በ FAP ሥር ለገንዘብ እርዳታ የተሟላ ማመልከቻ ካቀረበ ወይም ክፍያውን በሙሉ ከፈጸመ በኋላ ተጨማሪ መግለጫ መላክ አያስፈልግም። ከሚፈለጉት 3 ደብዳቤዎች ውስጥ በመጀመሪያው እና በመጨረሻው መካከል ቢያንስ 60 ቀን ማለፍ ይኖርበታል። አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ወይም ወደ ሌላ ቦታ በሚዛወርበት ጊዜ ትክክለኛ የመልዕክት አድራሻ መስጠት የታካሚው ግዴታ ነው። አንድ መለያ ትክክለኛ አድራሻ ከሌለው፣ ታካሚውን ለማግኘት የሚያስችሉ አማራጭ ዘዴዎች መኖር አለመኖራቸውን ሰራተኛው ይወስናል። ሁሉም የራስ-ክፍያ ሂሳቦች የነጠላ ታካሚ የሂሳብ መግለጫዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፤ ሆኖም በዚህ የተገደቡ አይደሉም፡-
    1. በመግለጫው-የመጀመሪያ መግለጫ ብቻ-የተሸፈኑ አገልግሎቶች ትክክለኛ ማጠቃለያ
    2. የክፍሉን ስልክ ቁጥር እና የተለያዩ ሰነዶች ሊገኙ የሚችሉበትን ቀጥተኛ የድረ ገጽ አድራሻን ጨምሮ በሆስፒታሉ FAP ስር የገንዘብ እርዳታ ማግኘት እንደሚቻል ለታካሚዎች የሚያሳውቅ እና የሚያሳስብ የጹሑፍ ማስታወቂያ።
B. አንድ ታካሚ የእሱን/የእሷን ሂሳብ በተመለከተ የሚከራከሩ ከሆነ እና/ወይም የክፍያ መጠየቂያውን በተመለከተ ሰነድ የሚጠይቁ ከሆነ፣ Fairview በ 7 ቀናት ውስጥ የተጠየቀውን ሰነድ በጽሑፍ ያቀርባል። በ 7 ቀን ምላሽ መስጠት የማይቻል ከሆነ፣ የእውቅና ደብዳቤ በ 7 ቀናት ውስጥ ይላካል፣ እናም በቅሬታ አቤቱታ ፖሊሲ መሰረት ምላሹ ከተላከበት ቀን አንስቶ ተጨማሪ አሰባሰብ ከመቀጠሉ በፊት ሂሳቡ ለ 30 ቀናት ያህል እንደተያዘ ይቆያል። ከላይ የተመለከቱት የምላሽ ደረጃዎች በ Fairview ሰብሳቢ ኤጀንሲዎች እና ሰብሳቢ ጠበቆች ላይም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።
C. የታካሚ እንክብካቤ ስጋቶች ለታካሚው መፍትሄዎች እና ምላሽ ለመስጠት በታካሚ የቅሬታ አቤቱታ ሂደት በኩል ይስተናገዳሉ። ሂሳብ(ቦች) እንደ አስፈላጊነቱ ይያዛሉ።
D. Fairview የሂሳብ መግለጫዎችን፣ ደብዳቤዎችን እና የስልክ ጥሪዎችን በመጠቀም ያልተከፈሉ ሂሳቦችን ለመፍታት ታካሚዎችን ለማነጋገር ከፍተኛ የክትትል ጥረት ያደርጋል፤ ይህም ታካሚው ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ብቁ ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ በንቃት መከታተልን ይጨምራል። በዚህ ሂደት ውስጥ ሂሳቦች መፍትሄ ካላገኙ፣ ያልተከፈሉት ሂሳቦች እንዲሰበሰቡ በሶስተኛ ወገን ለሚተዳደር ኤጀንሲ ወይም ጠበቃ ሊተላለፉ ይችላሉ።

III. ሕጋዊ አሰባሰቦች እና ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎች፡-

A. ለዚህ ፖሊሲ ድንጋጌዎች በሚኖር ተገዢነት ላይ በመመስረት፣ Fairview ለቀረቡት የሕክምና አገልግሎቶች ክፍያ ለማግኘት ሂሳቦችን በሕጋዊ አሰባሰቦች ስር ሊያስቀምጥ እና ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎችን ጨምሮ ማንኛውንም እና ሁሉንም ሕጋዊ እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል።
B. ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎች እንደሚከተለው ሊጀምሩ ይችላሉ፡-
    1. ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎች (ECAs) ከመወሰዳቸው በፊት ለታካሚ ከተሰጠው የመጀመሪያው ድህረ-አገልግሎት የክፍያ መጠየቂያ ቢያንስ 120 ቀናት ይሰጣል፣ በተጨማሪም Fairview ከዚህ መግለጫ ቀን ጀምሮ ታካሚው በ FAP ስር ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ እንዲያመለክት ቢያንስ 240 ቀናትን ይሰጣል።
    2. ሕጋዊ አሰባሰቦች ከመጀመራቸው በፊት አንድ ታካሚ በ FAP ሥር ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ካመለከተ፣ Fairview ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎች (ECAs) ከመጀመራቸው በፊት የታማሚውን ብቁነት መወሰን አለበት። ታካሚው ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ ቀድሞውኑ የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ውሳኔ ካለው የታካሚው ሁኔታ ወደ አዲስ ውሳኔ በሚፈልግ መልኩ ካልተለወጠ በስተቀር ይህ ቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ ጥቅም ላይ ይውላል።

3. ሂሳቦችን በሕጋዊ አሰባሰቦች ስር ከማስቀመጥ በፊት፣ ከሕጋዊ አሰባሰቦች መያዝ ያለበት ማንኛውም ሂሳብ መኖሩን ለመወሰን Fairview ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ጠቋሚ ማጣሪያ ያከናውናል። በሕጋዊ አሰባሰቦች ስር ለተቀመጡ ሂሳቦች፣ በመጀመሪያ Fairview ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎች (ECAs) የታቀዱ መሆኑን የሚገልጽ የጽሑፍ ማሳወቂያ ለታካሚው ማቅረብ አለበት። ይህ ማሳወቂያ በግልጽ ቋንቋ የቀረበ የ FAP ማጠቃለያን የሚያካትት ሲሆን ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎች (ECAs) ከመጀመራቸው ቢያንስ 30 ቀናት ቀደም ብሎ የሚቀርብ ይሆናል። በዚህ የ 30 ቀናት መስኮት፣ Fairview ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎች (ECAs) የታቀዱ መሆኑን ለታካሚው በቃል ለማሳወቅ እና ስለ Fairview የፋይናንስ እርዳታ ፖሊሲ ለታካሚው ለማሳወቅ ተገቢ ጥረቶችን ማድረግ አለበት። ለዚህ በቃል ለማሳወቅ ለሚደረገው ምክንያታዊ ጥረት አንድ ምሳሌ ለታካሚው መደወል እና የድምጽ-መልዕክት መተውን ያጠቃልላል።
4. በሕጋዊ አሰባሰቦች ስር ከተቀመጠ በኋላ፣ የገቢ አሰባሳቢ ጠበቃዎቹ እንደ የፍርድ ሂደት እርምጃዎች፣ የደመወዝና የባንክ እገዳዎችን ማስፈጸም፣ እና ሌሎች በሕግ የተደነገጉ የመሰብሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም፣ ያሉ ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎችን የማካሄድ ስልጣን ይሰጣቸዋል፤ ይሁን እንጂ የመጀመሪያዎቹ ክሶች ከመጀመራቸው በፊት የታካሚ የፋይናንስ አገልግሎቶች የቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። እንደነዚህ ያሉ ተግባራት የሚፈጸሙት በሁለቱ አካላት መካከል በተደረጉ ኮንትራቶች ውስጥ በተገለጸው በ Fairview ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የአሰባሰብ ደረጃዎች ስምምነቶች መስፈርቶች መሰረት ይሆናል።
5. አንድ ታካሚ ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎች (ECAs) በሂደት ላይ እያሉ በቅን ልቦና ላይ በመመስረት ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ማመልከቻ ካቀረቡ፣ ማመልከቻው በሚታይበት ወቅት እና የመጨረሻ ውሳኔ እንስከሚሰጥ ድረስ Fairview ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎችን (ECAs) ባሉበት ለማቆም የሚቻሉትን ጥረቶች ያደርጋል።

IV. የደምበኞች አገልግሎት፦

የሒሳብ አከፋፈል እና አሰባሰብ ሂደት ወቅት፣ Fairview እና ወኪሎቹ የሚከተሉትን መመሪያዎች ተግባራዊ በማድረግ ጥራት ያለው የደንበኞች አገልግሎት ይሰጣሉ፦

- Fairview እና ወኪሎቹ በሰራተኞቹ ለሚፈጸም የሚበድል፣ ተንኳሽ፣ አስጸያፊ፣ አሳሳች ወይም አታላይ የሆነ ቋንቋ ወይም ጠባይ ምንም ትዕግስት የማይኖርበትን አሰራር ተግባራዊ ያደርጋሉ።
- Fairview እና ወኪሎቹ የታካሚ ጥያቄዎችን እና/ወይም አለመግባባቶችን ለመቀበል ታካሚዎች ሊደውሉ የሚችሉበት ከክፍያ ነፃ የሆነ የስልክ ቁጥር እና ደብዳቤ ሊጽፉበት የሚችሉበት አንድ ታዋቂ የሥራ ቢሮ አድራሻን ጨምሮ አመቺ ሂደቶች እንዲኖሩ ያደርጋሉ። ይህ መረጃ በ Fairview በሚላኩ ሁሉም የታካሚ ሂሳብ መጠየቂያዎች እና የአሰባሰብ መግለጫዎች ላይ እንደተዘረዘረ ይቆያል።
- ከታካሚ የመጣ ግንኙነት ከተቀበሉ በኋላ፣ Fairview እና የወኪሎቹ ሰራተኞች በተቻለ መጠን በአፋጣኝ ወደ ታካሚዎች የስልክ ጥሪ ይመለሳሉ (ሆኖም ግን ጥሪው ከተደረገ ከአንድ የስራ ቀን በማይበልጥ ጊዜ) እና በቅሬታ አቤቱታ ሂደት መሰረት ለሚቀርቡ የጽሁፍ ክርክሮች በ7 ቀናት ውስጥ ምላሽ ይሰጣል።
- Fairview እና ወኪሎቹ የታካሚ አቤቱታና ቅሬታዎች (በቃል ወይም በጽሁፍ) መዝገብ ጠብቀው ያቆያሉ።

V. የፖሊሲ ተገኝነት፦

- የ Fairview የሂሳብ አከፋፈል እና አሰባሰብ ፖሊሲ፣ Fairview የፋይናንስ እርዳታ ፖሊሲ፣ እና የኛ የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ማመልከቻ ቅጽ የኤሌክትሮኒክ ቅጂዎች በድረ ገጻችን፡ www.fairview.org/billing. ላይ ማግኘት ይቻላል።
- በተጨማሪም የፖሊሲ ቅጂ እንዲላክልዎት ለመጠየቅ ወይም የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ማመልከቻ እና የብቁነት ሂደትን በተመለከተ ለመወያየት ከማዕከላዊ የሥራ ቢሮዎቻችን አንዱን ማናገር ይችላሉ።
    - Fairview የጤና አገልግሎቶች በ 612-672-6724 ወይም ከክፍያ ነፃ በ 1-888-702-4073
    - HealthEast እንክብካቤ ስርዓትን (HealthEast Care System) በ 651-232-1100 ወይም ከክፍያ ነፃ በ 1-866-770-6411
    - Fairview Range የሕክምና ማዕከልን በ 218-362-6624 ወይም ከክፍያ ነፃ በ 1-877-390-6624
- የፖሊሲዎቻችን እና የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ማመልከቻ ቅጽ የወረቀት ቅጂዎችን በክፍያ መጠየቂያ ቢሮዎቻችን እና በእያንዳንዱ የሆስፒታል ቦታ ማግኘት ይቻላል።
    - 750 E 34th Street, Hibbing, MN 55746
    - 1601 Golf Course Road, Grand Rapids, MN 55744

**በእነዚህ ብቻ ባይወሰንም፣ ያጸደቁ አካላት የሚከተሉትን ያካትታል፦**

Fairview Lakes የሕክምና ማዕከል ይህንን ፖሊሲ አጽድቋል።
Fairview የሕክምና ግሩፕ ይህንን ፖሊሲ አጽድቋል።

Fairview Northland የሕክምና ማዕከል ይህንን ፖሊሲ አጽድቋል።
Fairview Range የሕክምና ማዕከል ይህንን ፖሊሲ አጽድቋል
Fairview Ridges ሆስፒታል ይህንን ፖሊሲ አጽድቋል።
Fairview Southdale ሆስፒታል ይህንን ፖሊሲ አጽድቋል።
University of Minnesota የሕክምና ማዕከል፣ Fairview ይህንን ፖሊሲ አጽድቋል።
Grand Itasca ክሊኒክ እና ሆስፒታል ይህንን ፖሊሲ አጽድቋል
HealthEast Bethesda ሆስፒታል ይህንን ፖሊሲ አጽድቋል።
HealthEast St. John's ሆስፒታል ይህንን ፖሊሲ አጽድቋል።
HealthEast St. Joseph's ሆስፒታል ይህንን ፖሊሲ አጽድቋል
HealthEast Woodwinds ሆስፒታል ይህንን ፖሊሲ አጽድቋል
HealthEast ክሊኒኮች እና ሌሎች ከታክስ ነፃ የሆኑ አካላት ይህንን ፖሊሲ አጽድቀዋል።

**የፖሊሲ ባለቤት፡**

System Director, Revenue Cycle

**የጸደቀው፡**

በ Fairview የዳይሬክተሮች ቦርድ (Fairview Board of Directors)

**ቀን(ናት)፡**

**የሚጸናበት ቀን፡** 4/1/05

**የተከለሰበት ቀን፡** 4/03/12, 6/27/13, 3/5/14, 3/1/15, 2/1/16, 7/24/17, 6/20/19, 2/10/20, 2/1/21

**የተከለሰበት ቀን፡** የ Fairview ቦርድ ከልሶ እንደገና አጸደቀ: 5/7/15, 6/17/16, 8/17/17, 11/5/19, 8/5/21

**ተግባራዊ የሆነበት ቀን፡** 4/24/14, 5/7/15, 6/17/16, 11/1/17